# የሰሜን ጎንደር አስተዳደር ለሶስት የመከፈሉ ጉዳይ ለምን ይህን ያህል ትኩረት ሳበ?

ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ

ነሀሴ 29/2009 ዓ.ም

ስለጎንደርና አካባቢው ሲነሳ በርካታ ታሪካዊ ሁኔታዎች አብረው መታወሳቸው አይቀርም፣ ከእነዚህም መካከል አንደኛውና ዋነኛው ጉዳይ ጎንደር የቋረኛው ካሳ (የኋለኛው አጼ ቴውድሮስ አገር መሆኑ ሲሆን፣ የፋሲል ግንብ፣ የአጼ ዮሓንስ በመተማ ዮሓንስ ከድርቡሾች ጋር በቆራጥነት ሲዋጉ መስዋዕት መሆን እና የመሳሰሉት ታሪካዊ ክስተቶችም ግምት ውስጥ መግባተቸው የግድ ነው፡፡ ከዛም አልፎ የደጃች ውቤና የራስ አሊ ፍጥጫ በመጨረሻም የደጃች ካሳ (አጼ ቴውድሮስ) አሸናፊነትን ተከትሎ ጃን አሞራ ውስጥ በምትገኘው ደረስጌ ማሪያም ዘውድ ደፍተው የመንገሳቸው ሁኔታ ትውስ ማለቱ አይቀርም፡፡

ለመንደርደሪያ ይህን ያህል ካልሁ በኋላ በርዕሱ ላይ ወደ ተጠቀሰው ወቅታዊ ጉዳይ ልመለስና የተወሰኑ ሀሳቦችን አንስቼ ያገኘሁትን መረጃ ለተደራሲያን ላካፍል፣ ምክንያቱም እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአጠቃላይና ለአካባቢው ቅርበት እንዳለው ሰው በተለይ ጉዳዩ እኔንም ያገባኛል ብየ ስለማምን ምንድነው ነገሩ በማለት የጎንደርና አከካባቢውን ሰው ለመጠየቅ ሞክሬ ነበርና ነው፡፡

የቀድሞው ጎንደር ክፍለ ሀገር የአሁኖቹ የደቡብና የሰሜን ጎንደር አስተዳደር አካባቢዎች በቀደመው ዘመን ማለትም ከአንድ መቶ አምሳ አመታት በፊት ከአጼ ቴውድሮስ ወደ ስልጣን መምጣት ቀደም ብሎ በዘመነ መሳፍንት መሆኑ ነው በሶስት የአስተዳደር አካባቢዎች የተከፋፈለ እንደነበር ይታወቃል፡፡ እነዚህም ደንንያና አካባቢው በደጃች ማሩ ይገዛ ነበር፣ ቤጌምድር በመባል የሚታወቀውና በአሁኑ ወቅት በዋነኛነት ደቡብ ጎንደር ተብሎ የሚጠራው በራስ አሊ ይተዳደር ነበር፡፡

እንዲሁም በአሁኑ ወቅት በትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኘውን ሽሬና አካባቢውን ጨምሮ የሰሜን አውራጃ (አሁን ላይ በአዲሱ አደረጃጀት ሰሜን ጎንደር የተባለው) በደጃች ውቤ ይተዳደር እንደነበር ታሪክ ይነግረናል፡፡ የኋላ ኋላ ደግሞ አጼ ኃይለ ስላሴ የተወሰኑ አውጃዎችን ወደ አንድ ማዕከል አሰበሰበው ጠቅላይ ግዛት ሲያቋቁሙ ከላይ የተጠቀሱት አካበቢዎች የበጌምድር ጠቅላይ ግዛት በሚል ሰያሜ አንድ ላይ ሆኑ፡፡ ደርግ ወደ ስልጣን በመጣበት ወቅት መጀመሪያ ላይ ስያሜውን በመቀየር የጎንደር ክፍለ ሀገር ከማለቱም በላይ በመጨረሻ የስልጣን ዘመኑ ባወጣው የኢህዴሪ ህገ-መንግስት የጎንደር ክፍለ ሀገርን ሰሜንና ደቡብ ብሎ ለሁለት የከፈለው ሲሆን ብአዴን/ኢህአዴግም ይህንን አደረጃጀት ላለፉት 25 አመታት ባለበት ሁኔታ አስቀጥሎት ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአማራ ክልል መንግስትና ገዥው ፓርቲ የሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር የቆዳ ስፋትና የህዝብ ብዛት በእጅጉ ስላሳሰበው ይመስላል ለሶስት ከፋፍሎ ለማስተዳደር ጥናት ሲያካሂድ ከቆየ በኋላ ባለፈው ሰኔ ወር የመጨረሻ ውሳኔውን በማስተላለፍ የሰው ሀይል ምደባውን በይፋ ሲያሳውቅ የድጋፍና የተቃውሞ ድምጾች እዚህም እዚያም መሰማት ጀመሩ፡፡

እኔም ታዲያ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርሁት ከአካባቢው ህዝብ ጋር ካለኝ ጥብቅ የሆነ ትስስር የተነሳና እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የአካባቢው ለሶስት መከፈል ዋነኛ ምክንያት ምን ይሆን? የዚህ የሀሳብ ፍጭት መንስኤስ ምን ሊሆን ይችላል? በእርግጥም ይኽ ውሳኔ በክልሉ መንግስት ከመወሰኑ በፊት የህዝቡ ሀሳብ ግምት ውስጥ ገብቶ ነበርን? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ሀሳቦች

አንስቼ ያለኝን ቅርበት በመጠቀም ጭምር ከተለያዩ አካላት መረጃ ለማሰባሰብ ሞክርሁ፣ በዚህም መሰረት ያረጋገጥሁት ነገር ቢኖር የሚከተለውው እውነት ነው፡

1. የሰሜን ጎንደር አስተዳደር አካባቢ በህዝብ ብዛትም ሆነ በቆዳ ስፋት ከክልሉ ብቻ ሳይሆን ከሀገሪቱ ትልቁ ዞን በመሆኑ (ከ4 ሚሊዮን በላይ የሚሆን ህዝብ የሚኖርበት ስለሆነና ቋራና መተማ ወረዳዎች ብቻ ስፋታቸው የአንድ መለስተኛ ዞንን ስለሚያክል)፣
2. ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አካባቢው ባለው የተፈጥሮ ጸጋ ምክንያት የክልሉ ብቻ ሳይሆን የፌዴራሉ መንግስት የስበት ማዕከል እየሆነ በመምጣቱ (በተለይም በግብርናው መስክ ሰፊና ድንግል መሬት ያለው መሆኑና ለእንስሳት እርባታም ሆነ ለደን ልማት በእጅጉ የተመቼ አካባቢ ስለሆነ)፣
3. አካባቢው በአምስት አግሮ ኢኮሎጂ ዞኖች የሚከፈልና ለተለያዩ ሰብሎች (ለገበያም ይሁን ለምግብ የሚሆኑ) በእጅጉ የተመቼ ቢሆንም በመንግስት በኩል እስካሁን ድረስ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት ባለመልማቱ ምክንያት፣
4. አካባቢው ከሱዳን ጋር በቀጥታ ከመዋሰኑ ጋር ተያይዞ የንግድና ምጣኔ ሀብታዊ ግንኙነቱ ከመቸውም ጊዜ በላይ እያደገ የመጣበት ሁኔታ መፈጠሩ (ለሰሜንና ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢ የደረቅ ወደብ አገልግሎት እንዲኖር የማድረግ አስፈላጊነት የግድ የሚልበት ሁኔታ መከሰቱ)፣
5. አካባቢው ከሱዳን ጋር በቀጥታ መዋሰኑ ብቻ ሳይሆን ከኤርትራ በቅርብ ርቀት ላይ ስለሚገኝ (ክልሎች በ1984 ዓ.ም እንደ አዲስ ከመዋቀራቸው በፊት አካባቢው ከኤርትራ ጋር በቀጥታ ይዋሰን እንደነበር ይታወቃል) የጸጥታ ችግሩም ያን የህል የከፋ በመሆኑ የክልሉን ከፍተኛ አመራር የቅርብ ድጋፍና ክትትል ማግኘት ስለሚገባው እና
6. የበርካታ ወረዳዎች ከጎንደር ከተማ በእጅጉ ርቀው መገኘታቸው (ለምሳሌ ቋራ፣ መተማ፣ አዲአርቃይ፣ በየዳ፣ ጃን አሞራ ወዘተ) ነዋሪዎች ፍትህ በመሻትም ሆነ በዞን ደረጃ ሊያገኟቸው የሚገቧቸውን አገልግሎቶች ለማግኘት በአማካይ ከሁለት መቶ ኪሎ ሜትር በላይ መጓዝ የግድ ስለሚላቸው ከፍተኛ እንግልትና ወጭ ያስከትልባቸው የነበረ በመሆኑ ይህንን አስቸጋሪ ሁኔታ በማስቀረት በቅርቡ አገልግሎቱን ለማሟለት የግድ ስለሚል ነው አካባቢው ለሶስት እንዲከፈል የተደረገው የሚሉት ምክንያቶች በማብራሪያነት መቅረባቸውን አስተውያለሁ፡፡

ታዲያ ይህ ሲሆን የህዝቡ፣ በየደረጃው የሚገኙት የአመራር አካላትና የመንግስት ሰራተኞች ተሳትፎስ ምን ይመስል ነበር? እና ሀሳባቸውስ በምን መልኩ ተስተናገደ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመረጃ ሰጭዎቼ አንስቼላቸው የሰጡት መልስ ሲጨመቅ ደግሞ የሚከተለውን የሚመስል ሆኖ አገኘሁት፣ በዚህም መሰረት፡

ሀ. በዞኑ ውስጥ ከሚገኙት ከ520 በላይ የቀበሌ ነዋሪዎችን ለማወያየት ሲሞከር አላፋና ጣቁሳ አካባቢ የሚገኙ 7 ቀበሌዎች ብቻ የተለየ ሀሳብ አንስተው የነበረ ከመሆኑ ውጭ ሌሎቹ ግን እንዳውም ጉዳዩ የዘገየ ከመሆኑ ውጭ ሀሳቡን እንደግፈለን በሚል መልኩ በመስማማታቸው፣

ለ. ከ500 በላይ እንደሆነ ከሚገመተው የወረዳና የዞን አመራር ውስጥ ከተወሰኑት አባላት በስተቀር አሁንም አብዛኛው አመራር ሀሳቡን የደገፈውና ለተግባራዊነቱም በግንባር ቀደምነት ለመንቀሳቀስ ዝግጁ መሆኑን በማረጋገጡ፣

ሐ. የዞኑ የመንግስት ሰራተኛ በተወያየበት ወቅት የተወሰኑ ግለሰቦች ይኽ ውሳኔ በቅርቡ የተከሰተውንና አሁንም ድረስ ብቅ ጥልቅ በማለት የክልሉን መንግስት ረፍት የነሳውን የህዝብ ተቃውሞ ለማዳከምና የወልቃይትን የአማራ ማንነት ጥያቄ አቅጣጫ ለማስቀየር ስለተፈለገ ነው የሚል ሀሳብ ተነስቶ የነበረ ቢሆንም አብዛኛው ግን የስምምነት ሀሳቡን በመግለጹ እና

መ. የሁሉም ወረዳ ምክር ቤቶች በመደበኛ ስብሰባቸው ላይ ጉዳዩን በአጀንዳነት ይዘው ከተወያዩ በኋላ በአብላጫ ድምጽ ሀሳቡን ደግፈው መወሰናቸው በመረጋገጡ ምክንያት የክልሉ መንግስት አስተዳደር ምክር ቤት የሰሜን ጎንደር አካባቢ ከሶስት ተከፍሎ እንዲደራጅ ወስኖ ካለፈው ሰኔ ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ ለአዳዲሶቹ ዞኖች የሰው ሀይል እንዲመደብ አድርጓል፡፡ እንግዲህ እውነታው እንደዚህ ከሆነ የሰሞኑ ክርክር ጉንጭ አልፋ ብቻ ሳይሆን ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ መሆኑ ነው፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ሌላው ጉዳይ ደግሞ የቅማንት የማንነትና የራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄና የክልሉ መንግስት ምላሽ ነው፡፡ ቅማንቶች የተለየ ማንነት እንዳላቸውና ይህም የተለየ ማንነታቸው ህጋዊ እውቅና ሊሰጠው እንደሚገባ ጥያቄ ማንሳት የጀመሩት ከ1984/5 ዓ.ም ጀምሮ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡

ይህም ሆኖ ጉዳዩ የአብዛኛውን የቅማንት ህዝብ ብቻ ሳይሆን የልሂቃኑን ጠንካራ ድጋፍ ማግኘት ባለመቻሉ ምክንያት ጥያቄው ለበርካታ አመታት ሲነሳና ሲወድቅ ለመቆየት ተገዷል፡፡ ሆኖም በ1999 ዓ.ም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን አማካኝነት በተካሄው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ በሀገሪቱ ከሚገኙ ብሔረሰቦች ዝርዝር ውስጥ የቅማንት ብሔረሰብ እንዲወጣ ተደርጎ በመቅረቡ ሳቢያ የብሔረሰቡን ምሁራን በእጅጉ አስቆጥቶ በተደራጀ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ አደረጋቸውና የአማራ ክልል አመራርን እረፍት አሳጥቶ ሰነበተ፡፡

ከዛም አልፎ የክልሉ መንግስት አፋጣኝ ምላሽ ባለመስጠቱ ምክንያት ሰሜን ጎንደር ውስጥ በሚኖሩ አማሮችና ቅማንቶች መካከል ዘመናትን ያስቆጠረው መልካም ማህበረ-ምጣኔ ሀብታዊ ግንኙነት በአጭር ጊዜ እንቅስቃሴ ሻክሮ በሒደትም ወደ ግጭት አመራና የበርካታ ሰው ህይወት ከማጥፋቱም በላይ በአካባቢው ለተፈጠረው አለመረጋጋት ምክንያት ሆኗል፡፡

በመጨረሻም የክልሉ አመራር በእጅጉ ተገፍቶና ተላልጦም ጭምር በሒደት የቅማንትን ማንነት እውቅና ከመስጠት አልፎ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ የሚያደርግ አዋጅ እንዲያጸድቅ መገደዱ አልቀረም፣ ስለሆነም የቅማንት የማንነትና ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ከሰሜን ጎንደር በሶስት መከፈል ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው ቢሆንም በአካባቢው ለተፈጠረው አለመረጋጋት ግን የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከቱ አልቀረም፡፡

ተጠቃሎ ሲታይ የሰሜን ጎንደር አስተዳደር አካባቢ ለሶስት በመከፈሉ ምክንያት የጎንደርን ህዝብ አንድነት ሆን ብሎ ለማዳከም ነው የሚለው ሀሳብ ያን ያህል ውሀ የሚያነሳ የመከራከሪያ ነው ብሎ ለመውሰድ ያስቸግራል፣ ምክንያቱ ደግሞ ከላይ በዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይ ለማንሳት እንደሞከርሁት የጎንደር አካባቢ ቀደም ሲል ጀምሮ በተለያየ አደረጃጀት ሲከፈልና ሲጠቃለል የነበረ ቢሆንም ጎንደሬነትን ሸርሽሮ በፍጹም ሲያዳክመው አልታየምና ነው፡፡ በሌላ በኩል አሁን የተፈጠረውን የህዝብ ተቃውሞ ለማዳከምና አቅጣጫ ለማስቀየር ነው የሚለው ክርክርም ብዙ ርቀት የሚያስኬድ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

ይህን ለማለቴም በቂ ምክንያት አለኝ፣ የህዝቡ ተቃውሞ መነሻም ሆነ መድረሻ የፍትህ እጦት፣ የመልካም አስተዳደር ችግር፣ የሙስና መስፋፋት እና የእኩል ተጠቃሚነት አለመኖር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፣ እነዚህ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ደግሞ የአስተዳደር ድንበር በማካለል ብቻ የሚፈቱና የሚደፈቁ ባለመሆናቸው ምክንያት በየትኛውም የአስተዳደር አካባቢ የሚገኘው ህዝብ በአንድ ላይ ተቃውሞውን የመግለጽና እስከመጨረሻው የመግፋት ዕድሉ ሰፊ ነው፣ ለዚህም ጥሩ ምሳሌ

የሚሆነው ባለፈው አመት ጎንደር ላይ የተነሳው ተቃውሞ ሳይውል ሳያደር ጎጃም ውስጥ ገብቶ ምድር አንቀጥቅጥ የሆነ ሰልፍን መጋበዙ ነው፡፡